መንፈሳዊነት ምንድን ነው?

በዲያቆን ያረጋል አበጋዝ

በዚህ ጽሑፍ መንፈሳዊነት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በአጭሩ, ለማየት እንሞክራለን።

፩. መንፈሳዊነት ማለት ከእግዚብሔር ጋር ያለ ኅብረትና አንድነት ነው።

መንፈሳዊነት መገለጫዎቹ ብዙና የተለያዩ ሊሆኑ ቢችሉም በዋናነት ሲጠቃለል ግን እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ማምለክ ማለት ነው፡ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል” እንዳለ። /ዮሐ.፬፥፳፬/ እንዲሁም ጌታችን ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው” በማለት እንዳስተማረን፤ መንፈሳዊ የሚባለው በጥምቀት ረቂቅ የሆነ መንፈሳዊ ልደትን ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ የተወለደ ብቻ ነው። ይህን ጸጋ ያላገኘ ሰው ጌታችን ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው” እንዳለው ከሥጋ ብቻ የተወለደ ስለሆነ ሥጋ ብቻ (ሥጋዊ ሰው) እንጂ መንፈሳዊነት የለውም።

ሕይወት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ማለት ሲሆን ሕይወት ከሆነው ከእግዚአብሔር መራቅና መለየት ደግሞ ሞት ነው። መንፈሳዊነት ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር በመኖር የሚገኘውን ሕይወት ገንዘብ ማድረግ ነው። መንፈሳዊነት የእግዚአ ብሔር የባሕርያቱ መገለጫዎች የሆኑትንና ለሰው በፍጥረት ጊዜ የተሰጡትን ጸጋዎች ገንዘብ ማድረ ግና ከመነሻነት ወደ ፍጹምነት ማሳደግ ነው።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር “ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ፤ ሰውን እንደ መልካችን፣ እንደ ምሳሌ ያችን እንፍጠር" ካለ በኋላ “እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው” ይላል። ይህም ማለት ሰው አርአያ (መልክአ) እግዚአብሔር እና አምሳለ እግዚአብሔር (ምሳሌ) ተሰጥተው ታል ማለት

ነው። ከእነዚህ የመጀመሪያውን (የእግዚአብሔር መልክ) በፍጥረት ጊዜ (ሲፈጥረው) ሰጥቶታል። “እግዚአብሔርም : ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው” ይላል:: ሁለተኛው የእግዚአብሔር ምሳሌ ግን ከእግዚአብሔር መልክ ተነሥቶ የተሰጠውን ጸጋ በማሳደግ ወደፊት ይደርስበት ዘንድ የተሰጠውና ገና ያልደረሰበት ነው።

አርአያ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር መልክ) የተባሉት በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት፤

በእግዚአብሔር ዘንድ በምልኣት ያሉት፣ ለሰው ደግሞ እንደ ዓቅሙ መጠን የተሰጡት፡- ቅድስና፣ ፍቅር፣ ጥበብ፣ ነጻነት፣ ገዢነት፣ እና የመሳ ሰሉት መንፈሳዊ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ለሰው በተፈጠረ ጊዜ የተሰጡት በዘርነት (በመነሻነት) ደረጃ ነው። እነዚህ የእግዚአብሔር መልክ የተባሉት የቅድስና መንፈሳዊ ባሕርያት መገለጫዎች ለሰው የተሰጡት ያሳድጋቸውና ይንከባከባቸው ዘንድ ነው። እነዚህን የማሳደጉና ወደ ፍጹምነት ደረጃ የመውሰዱ ሂደት ነው መንፈ ሳዊ ሕይወትና መንፈሳዊነት የሚባ ለው። በዚህም ሰው ከተሰጠው የእግዚአብሔር መልክ ወደ እግዚአ ብሔር አርአያ ያድጋል ማለት ነው። “...የሥጋችን አባቶች... መልካም ሆኖ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፥ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል” በማለት እንደ ገለጸው፤ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረበት ዋና ዓላማና በየጊዜው በእኛ ላይ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ግባቸው እኛ ከቅድስናው እንድንካፈል ማድረግ ነው። /ዕብ.፲፪፥፲/ “ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና” ያለው ለዚህ ነው። /ዕብ.፲፪ ፥ ፲፬/

ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባትና መምህር ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ይህን ሲያመሰጥርና ሲያስረዳ፤ መንፈሳዊነት ከአርአያ እግዚአብሔር ወደ አምሳለ እግዚአብሔር (From Image to Likeness) የሚደረግ የማደግ ሂደት ነው ይላል። ይህ የዕድገት ሂደትም የማያቋርጥና የማያቆም ነው። በፍጥረት ጊዜ የተሰጠን “አርአያ እግዚአብሔር” እንደ ዘር ሲሆን፤ በመንፈሳዊነት የዕድገት ሂደት ገንዘብ እናደርገው ዘንድ የተሰጠን

“አምሳለ እግዚአብሔር” ደግሞ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ እና መንፈሳዊነት እንደ ዛፍ ነው። አንድ ዘር ዛፍ፡

ለመሆን የሚያስችለው መሠረታዊ ባሕርይ ሁሉ አለው። ሆኖም ሙሉ ዛፍ ሆኖ ለማደግና ለማፍራት የሚያ

ስፈልጉት ብዙ ነገሮች (መተከል፣ ውኃ መጠጣት፣ መኮትኮት፣ የፀሐይ ብርሃን፣ ጊዜ) አሉ። እነዚህን ካገኘ ግን ዘሩ አድጎ ሙሉ ዛፍ ይሆናል፤ፍሬንም ይሰጣል። መንፈሳዊነትም እንደዚያ ነው። በተፈጥሮ እንደ ዘር የተሰጠንን አርአያ እግዚአብሔር በቃለ እግዚአብሔር፣ በፍቅረ እግዚአብሔር ፣በትሕትና ፣በምስጢራትና በተጋድሎ በማሳደግ ወደ አምሳለ እግዚአብሔር ደረጃ ማሳደግ ነው። ይህም ማለት እነዚህ ነገሮች በፍጹምነት ያሉት በእግዚአብሔር ዘንድ ሲሆን ሰው ደግሞ የተቻለውን ያህል በጸጋ ገንዘብ ሊያደርጋቸው ይችላል። ይህም ማለት መንፈሳዊነት የሚባለው ሰዎች በቅድስና፣ በፍቅር፣ በጥበብ፣ በነጻ ነትና በመሳሰሉት መንፈሳዊ ባሕርያት እያደጉ መሄድ ነው። እነዚህም እንደ ዘርና እንደ ቡቃያ ከትንሽ ጀምረው ቀስ በቀስ ሲያድጉ ቅድስናን ፍጹም ወደ ማድረግ ደረጃ እየተሸጋገሩ ይሄዳሉ።

ይህ መንፈሳዊ የዕድገት ሂደትም ቀጣይ ነው። ከሞት በኋላም ቢያንስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ይቀጥላል። እኛ ኦርቶዶክሳውያን ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩን ወገኖቻ ችችን ጸሎት የምናደርገውና የምናስባቸውም አንዱ ለዚህ ነው። መንፈሳዊ የዕድገት ሂደታቸው በሞት አይቋረጥም ብለን እናምናለን። በአንድምታ ትርጓሜው መቅድመ ወንጌል ላይ “ወይትዌሰክ ሎሙ ስን በዲበ ስን፤ በጸጋ ላይ ጸጋ እየተጨ መረላቸው ይሄዳል” የሚለውም ይህንኑ የሚያስረዳ ነው። ሐዋርያው “እንግዲህ ወዳጆች ሆይ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረ ግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ” በማለት እንደ ተናገረ። /፪ ቆሮ.፯ ፥ ፩/

እሥራኤል የተባለ ያዕቆብ በመንገድ ላይ ሳለ ባየው ራእይ ላይ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተዘርግቶ፣ የእግዚአብሔርም መላእ ክት ሲወጡበትና ሲወርዱበት፣ በመሰላሉ መጨረሻ ላይ ደግሞ እግዚአ ብሔር በላዩ ቆሞበት አየ። /ዘፍ.፳፰፥፲፪-፲፫/ ያ ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ ተዘርግቶ፣ ከመጨረሻው ላይም እግዚአብሔር ሆኖበት ያየው መሰላል የመንፈሳዊ ሕይወት ሂደትና ጉዞ አመልካች ነው። መንፈሳዊነትም በዚህ ዓለም ባለን ሕይወት ከወጣኒነት ጀምሮ ወደ ፍጹምነት፣ ከምድራዊነት ወደ ሰማያዊነት ፣ ከቁሳዊነትና ከሥጋዊነት ወደ መንፈሳዊነት የሚደረግ ጉዞ ነው። በመሰላሉ ጫፍ ላይ እግዚአብሔር ተቀምጦበት እንደ ታየው ሁሉ የመንፈሳዊ ጉዞ የመጨረሻ ግብና ዓላማም እግዚአብሔር ነው።

መንፈሳዊነት ከእግዚአብሔር ጋር መሆንና ከእርሱ ጋር ፍጹም ኅብረትን፣ ቅድስናን፣ ፍቅርን ገንዘብ ለማድረግ የሚደረግ ጉዞ ነው። ኃጢአት ማለት ደግሞ ከእግዚአብሔር ኅብረትና አንድነት መለየትና መራቅ ነው። ኃጢአት ከእግዚአብሔር የተሰጠንን መልክ (ቅድስና፣ፍቅር፣ ነጻነት፣ ጥበብ፣) እያጡ መሄድና እግዚአብሔር ያልፈጠረው ግን ከእርሱ መራቅ የሚወልደውን ሌላ ባእድ መልክ መያዝ ነው። ይህም ማለት ብርሃን ሲጠፋ ጨለማ፣ ጤና ሲታወክ ደዌ እንደሚሰፍነውና እንደሚሠለጥነውነማለት ነው። ጌታችን በወንጌል ላይ ጌጤ በጠፋባት ሴት ምሳሌ የተናገረው ስለዚህ ነው። /ሉቃ.፲፭፥፰-፱/ ያች ሴት ከዐሥሩ ጌጦቿ መካከል የጠፋባት አንዱ ድሪም ብቻ የነበረ ቢሆንም ባላት በዘጠኙ ጌጧ ደስ ሊላትና ልትጽናና አልቻለችም ነበር። ስለዚህም የጠፋባትን ዐሥረኛውን ጌጧን አጥብቃ ፈለገች፣ ባገኘችውም ጊዜ ስለማግኘቷ ጎረቤቶቿን ሁሉ እስከምትጠራ ድረስ ደስታው ፈነቀላት። ሰው እንደ ዘጠኙ ጌጥ የተለያየ ነገር (ሀብት፣ ንብረት፣ ሥልጣን፣...) ቢኖረውም አስረኛው ድሪም ተብሎ በምሳሌ የተገለጸው ዋናው ድሪም የሆነው መልክአ እግዚአብሔር በስንፍናና በኃጢአት ምክንያት ከጠፋበት እው ነተኛ ደስታን ሊያገኝ አይችልም።ለእግዚአብሔር ማረፊያ የተፈጠረው ልቡናውም ዕረፍትን አያገኝም። ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው ዕረፍትና ደስታ የሚያስገኘውንና በጸጋ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ድሪም የተባለ መልክአ እግዚአብሔርን መጠበቅና ወደ ፍጹምነት ማሳደግ አለበት። በኃጢአት ምክንያት ጠፍብቶን ከሆነም እስክናገኘው ድረስ አጥብቀን መፈለግ ይኖርብናል።

መንፈሳዊነት ማለት ይህን እግዚአብሔር የሰጠንን አርአያ (መልክ) መጠበቅ እና ከዚያም ከተሰጠን መልክአ እግዚአብሔር ወደ አምሳለ እግዚአብሔር መጓዝ ነው። ይህ ጉዞም የማያቋርጥ ሂደት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት የተናገረው ስለዚህ መንፈሳዊ ዕድገት ነው። “አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለእርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።” /ፊል. ፫ ፥ ፲፪-፲፬/

መንፈሳውያን በዚህ የመንፈሳዊነት የጉዞ መሰላል ላይ ይገኛሉ።አንዳንዶች በመሰላሉ በጣም ከፍ ብለው ብዙ ርቀት ሄደው ይሆናል፣ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ቅዱሳን ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ደናግል መነከሳት አሉ። ሌሎች ደግሞ

እንደየዓቅማቸውና መጠናቸው በመንፈሳዊነት ሂደት በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኙ ይሆናል። ማን የት ላይ እንዳለ የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው። ዋናው ነገር ግን መንፈሳዊ ሰው የሚባለው ወደ እግዚአብሔር በሚደረገው ጉዞ ቢያንስ ከምድር ከፍ ብሎ መሰላሉ ላይ የሆነ ደረጃ ላይ ያለ ሲሆን ነው።

፪. መንፈሳዊነት ስሜትን፣አእምሮንና መንፈስን ሲገዛ ነው።

በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ እነዚህ ሦስት ነገሮች ይኖራሉ። እነርሱም ስሜት (Emotion)፣ አእምሮ (Intellect)፣ እና መንፈስ(Spirit) ናቸው። ስሜት (Emotion) የሚባለው ሰው *ሥጋ* ለባሽ ከመሆኑና *ሥጋዊ* ደማዊ ሕይወት ያለው ከመሆኑ የተነሣ በሕይወቱ ውስጥ ያለ ነገር ነው።አእምሮ (intellect) የሚባለው ደግሞ ሰው በተሰጠው የአዋቂነት ጸጋ የሚያስብ፣ የሚመራመርና ክፉውን ከበጎው መለየት የሚያስችል ረቂቅ የማሰብ ችሎታ የተሰጠው መሆኑን የሚያመለክት ነው።በዚህ ጸጋውም ሰው በቅርብና በሩቅ ያሉትን ነገሮች የማሰብ፣ የማመዛዘንና የማሰላሰል ችሎታው ተጠቅሞ ያውቃል፣ ይወስናል፣ ወደ ሆነ አቋምና ድምዳሜም ይደርሳል። ከእነዚህ በተጨማሪ የሰው ልጅ መንፈስም (Spirit) አለው። ሰውን ከሌሎች ፍጥረታት የሚለየው ባለ አእምሮ መሆኑ ብቻ ሳይሆን መንፈሰ እግዚአብሔር በውስጡ ያለበትና መንፈሳዊ የመሆን ጸጋ የተሰጠው በመሆኑም ነው።

እነዚህ ሦስት ነገሮች በሰው ውስጥ መኖራቸው ተፈጥሮአዊ ነው። ነገር ግን የአንድን ሰው ማንነት የሚወስነው በውስጡ ከሚኖሩት ከእነዚህ ከሦስቱ ነገሮች መካከል የበላይ ገዢው፣ የሰውዬውን ሕይወት በበላይነት የሚቆጣጠረውና የሚመራው ማን ነው? የሚለው ነው። አንድ ሰው እንደ ግኡዛን ፍጥረታት ስሜት አልባ ሊሆን አይችልም። እንዲሁም የማያስብና በአእምሮው ዕውቀት የሌለው ሰው አይኖርም። የእንዳንዱን ሰው ማንነት የሚወስነው ግን ከእነዚህ ከሦስቱ የበላይ ሆኖ ሰውዬውን የሚቆጣጠረው ነው። ሰውዬውን የሚመራው ስሜቱ ነው? ወይስ በአእምሮው የሚያወጣውና የሚያወርደው አለኝ የሚለው ዕውቀቱ? ወይስ መንፈሰ እግዚአብሔር?

አስተሳሰቡን፣ ድርጊቱንና በአጠቃላይ እርሱነቱን ስሜቱ (Emotion) የሚነዳውና የሚያዝበት ሰው ስሜታዊ እንጂ መንፈሳዊ አይደለም። በአእምሮው ብቻ የሚመራም አእምሮአዊ (Intellectual) ሰው ብቻ ነው። ሕይወቱን ሁሉ፤ስሜቱን፣ አእምሮውን፣ አስተሳሰቡንና ዕውቀቱን፤ የሚመራው መንፈሰ እግዚአብሔር የሆነ ሰው ደግሞ መንፈሳዊ ይባላል። መንፈሳዊ ሰው ማለት በተፈጥሮው ስሜት የሌለው፣ በአእሮውም የማያስብና የተለየ ተፈጥሮ ያለው ሰው ማለት አይደለም። ስሜቱንና ሁለንተና ውን በእግዚአብሔር መንፈስ የሚያ ስገዛ ሰው ማለት እንጂ።

መንፈሳዊ ሰው የሚሠራው ሥራ ምንም ይሁን ምን፣ (ግብርና፣ ንግድ፣ ፋብሪካ፣ አገልግሎት... . .)፣ በሕይወቱ በሚያልፍባቸውና በሚገ ጥሙት የተለያዩ የሐዘንም ይሁን የደስታ ውጣ ውረዶች (ጋብቻ፣ ሞት፣ ሐዘን፣ ደስታ...) ሁልጊዜም ቢሆን ስሜቱ ጭልጥ አድርጎ አይወስደውም። ስሜቱ ሊያሸንፈው ቢስበው እንኳ ቆም ብሎ ሁሉንም ነገር ከመንፈሳዊነት ሚዛንና አቅጣጫ አንጻር ለመቃኘትና ለመቆጣጠር ይታገላል።

አንዳንድ ጊዜ ስሜት አሸንፎት ወይም ደግሞ አእምሯዊነት ሠልጥኖበት ድቀትና መሰናክል ቢገጥመው እንኳ ይህ የሕይወት ሂደት የሚያመጣው መሆኑን በመገንዘብ ወደ መንፈሳዊነት ጎዳናው በንስሐ በቶሎ ይመለሳል። ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው ማለት ሥጋ ያልለበሰ፣ ስሜት የሌለው፣ በአእምሮው የማይ ጠቀም፣ ወይም በዚህ ዓለም ያሉ ሌሎች ሰዎች የሚሰማቸውና የሚያስቡት ነገር ለእርሱ የማይሰማውና የማይታሰበው፣ በሌሎች የሚደርስ ፈተናም የማያገኘው ማለት አይደለም። እነዚህን ሁሉ በመንፈሰ እግዚአብሔር መነጽር የሚያይና የሕይወቱ ማጠንጠኛ መንፈሳዊነት የሆነ ማለት ነው። ሐዋርያው “እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና በማለት እንዳ ስተማረን :: ” /ሮሜ.፰ ፥፲፫-፲፬ / ስ ለ ዚ ህ መንፈሳዊነት በስሜት ወይም በራስ ዕውቀት ሳይሆን በመንፈሰ እግዚአብሔር መመራት ነው።

፫. መንፈሳዊነት ጥረት፣ተጋድሎ፣ ውጣ ውረድ ነው

መንፈሳዊነት ሂደት እንደመሆኑ መጠን በአንድ ጊዜ የሚደረስበትና የሚጠናቀቅ ጉዞ ሳይሆን በዚህ ዓለም በተሰጠን የዕድሜ ዘመን ሁሉ የምንጓዘው ትዕግሥትንና ጽናትን የሚጠይቅ ረዘም ያለ ጉዞ ነው።በዚህ ጉዞ ውስጥ መንፈሳዊነትን የሚፈታተኑ፣ በስሜትና በአእምሮ አዊነት ስሌት ብቻ እንድንጓዝና ሥጋዊነት እንዲያይልብን ለማድረግ ወደ ታች ወደ ምድራዊነት የሚስቡን የተለያዩ ውስጣዊና አፍአዊ ፈተናዎች ይኖራሉ። መንፈሳዊነት ከእነዚህ ጋር መታገልና ማሸነፍ ነው። ለመንፈሳዊ ጉዞ ጥሩ ምሳሌና ማሳያ ተደርጎ የተሰጠን የእሥራኤላውያን ጉዞ ነው። እነርሱ ከግብጽ እንደ ወጡ ወዲያውኑ ቀይ ባሕርን ተሻግረው የተስፋዪቱ ምድር ከነዓን አልገቡም። ከግብጽ ወጥተው ቀይ ባሕርን በተአምራት ከተሻገሩ በኋላ ራሳቸውን ያገኙት የሚያቃጥልና በጣም ከባድ በሆነው በሲና በረሓ ውስጥ መጓዝ እንዳለባቸው ነበር። ከዚያም ለአርባ ዓመታት ያህል በተለያዩ ፈተናዎች ሲፈተኑ ቆይተው ከብዙ ውጣ ውረድና መንከራተት በኋላ ነበር ወደ ከነዓን የገቡት።

ምሳሌያዊና ምድራዊ ለሆነችው ለከነዓን ምድር ያን ያህል አስቸጋሪ ተጋድሎና ውጣ ውረድ የሞላበት የአርባ ዓመት ጉዞ ማድረግ ያስፈለጋቸው ከሆነ ሰማያዊና ዘለዓለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስማ ምን ያህል የበለጠ መፈተንና ፈተናን በትዕግሥት መወጣት ይገባን ይሆን? ስለሆነም በመንፈሳዊ ሕይወት ለመጓዝና መንፈሳዊ ለመሆን በመጀመሪያ ፈተና እንዳለ ማወቅ፣ ከዚያም ሲመጣ አለመደናገጥና እግዚአብሔርን በመማጸን መታገል የግድ ነው።

በዚህ የመንፈሳዊነት ሂደት የተለያዩ መቁሰሎችና መሰናክሎች ሊደርሱ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም ግን አንድ ወታደር ወደ ጦርነት ሲገባ ሊቆስል ወይም ሊሞት እንደሚችል አስቀድሞ አውቆ እንደሚያደርገው ሁሉ መንፈሳዊ ሰውም የሚገጥመውን የኃጢአት ቁስል የተጋድሎው ሂደት ያመጣው መሆኑን በመገንዘብ ተስፋ ሳይቆርጥ ቁስሉ የሚያገግምበትን ነገር ማድረግ ይኖርበታል። እነዚህም ንስሐ መግባትና ከምስጢራት መካፈል ናቸው።ከዚያም መንፈሳዊ ጦርነቱን እንደገና መልሶ ሊቀላቀል ይችላል። ይልቁንም አንድ ወታደር የሚነቀፈው በጦር ሜዳ ላይ በመሞቱ ወይም በመቁሰሉ አይደለም። የተማረከ ወይም የሸሸ እንደ ሆነ ነው እንጂ።መንፈሳዊ ሰውም የሚነቀፈው ፈርቶ ከመንፈሳዊ ተጋድሎ ወደ ኋላ የሸሸ ወይም በኃጢአት የተማረከና ከመንፈሳዊነት ጎዳና የወጣ እንደ ሆነ ነው እንጂ በተጋድሎ ሂደት በመቁሰሉ አይደለም። በተጋድሎ ሂደት መቁሰል እንዲያውም የመንፈሳዊ አርበኛነትና የተጋዳይነት መገለጫና መለያ ነው።

መንፈሳዊ ሕይወት ከራስ ጋርና ከልዩ ልዩ ፈተናዎች ጋር መታገልና መጋደል መሆኑ የታወቀ ነው።ማንም ሰው ሳይፈተንና ፈተናዎችን ሳያልፍ በመንፈሳዊ ሕይወት መኖርና ማደግ አይችልም። ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ራሱን አብነት አድርጎ ሲናገር “የሚደክም ማን ነው፥ እኔም አልደክምምን? የሚሰናከል ማን ነው፥ እኔም አልናደድምን?” በማለት እንደ ገለጸው። /፪ቆሮ.፲፩ ፥ ፳፱/ ቅዱስ ያዕቆብም በመልእክቱ “እነሆ፥ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፥ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታች ኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና” በማለት ተፈትነው ያለፉትን አብነት እንድናደርጋቸው ያስታ ውሰናል። ከዚያም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከታላላቅ መዓርግ የደረሱት ሁሉም እንደ እኛ ሰዎች የነበሩና በሰው ላይ የሚደርሰው ሁሉ የሚደርስባቸው ሆነው ሳለ ያን በተጋድሎ ያለፉ መሆናቸውን ለማዘከር ሲል “ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ፣ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች” በማለት ጽፏል። ፭፥፲፯-፲፰

ከዚህም ጋር መንፈሳዊነት ቁርጠኝነትንና ውሳኔን ይጠይቃል። ለዚህ ነው ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱና በአጠቃላይ እርሱን መከተል ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው ሁሉ ጥሪውን እንዲህ ሲል ያቀረበው። “ዘይፈቅድ ይትልወኒ፤ ይጽላእ ርእሶ ወያጥብእ ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ ወይትልወኒ- እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ፣ በመጨከንም መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ።” /ማቴ.፲፮፥፳፬/ ከሁሉም በፊት ራሱን ያልካደ ሰው፣ ከዚያም ያልጨከነ ሰው የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል መሸከምና እርሱን መከተል አይችልም። ያለዚያ እንዴት ተደርጎ ይቻላል? ስለዚህም የልብ ጥብዓት ለመንፈሳዊነት ወሳኝ ነው። ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ ደጋግሞ “ጥቡእ ልብየ እግዚኦ፤ አቤቱ ልቤ ጨካኝ ነው፥ አቤቱ፥ ልቤ ጨካኝ ነው እቀኛለሁ፥ እዘምራለሁ” እያለ የዘመረው ለዚህ ነው። /መዝ.፶፮፥፯ ፹፯፥፩/ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ አጠራሩና ከኦሪት ወደ ወንጌል እንዴት እንደ ተመለሰ ሲገልጽ፤“ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም ብሏል። /ገላ.፩፥፲፩-፲፮/

፩. መንፈሳዊነት ጊዜና ቦታ የማይወስነው ነው።

አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ መሆን ባለፉት ዘመናት ብቻ ይቻል የነበረ እንጂ አሁን እኛ ባለንበት ዘመን የማይቻል ነገር እንደ ሆነ አድርገው ሲያስቡና ሲናገሩ ይሰማሉ። ነገር ግን በየትኛውም ዘመን ቢሆን ክፋትና መሰናክል ያልነበረበት አንዳ ችም ዘመን አልነበረም። እንዲያውም ካለፉት ዘመናት በብዙዎቹ ላይ የነበረው የፈተና ክብደትና ጥልቀት እኛ ካለንበት ዘመን ይልቅ በጣም ግዙፍ ነው። የደረሰባቸውን ፈተና ለመቀበል ቀርቶ በሌሎች ላይ ይደርስ የነበረውን እንኳ ለማየት እጅግ ዘግናኝ የነበረባቸው ዘመናት ነበሩ። የመጀመሪያዎቹን ሦስት መቶ ዓመታት፤ ‹‹ዘመነ ሰማዕታትን - ክርስቲያኖች በምን ዓይነት ሁኔታ እንዳሳለፏቸው ማስታወስ›› ለዚህ በቂ ነው።

እንዲያ ሆኖም ግን በየዘመናቱ የነበሩትን ፈተናዎችና ለመንፈሳዊነት የማይመቹ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አልፈው አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉና በእግዚአብሔር ዘንድ የተመሰከረላቸው ሰዎች ነበሩ። ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ሄኖክ ሲናገር እንዲህ እንዲል፡- “ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፣ እግዚአብሔር ወስዶታልና።” /ዘፍ.፭፥፳፬/ በሰብአ ትካት ዘመን ኖኅ ከዚያ በንፍር ውኃ እስኪያጠፋው ድረስ የእግዚአብሔርን ቁጣ ካነሣሳ የመጨረሻ ክፉ ሕዝብ መካከል ጻድቅ ሆኖ ተገኝቷል። ቅዱስ መጽሐፍ “ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ፤ ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ” በማለት አንደ መሰከረለት። /ዘፍ.፮ ፥ ፱/

በእሥራኤላውያን የሃይማኖት ታሪክ ውስጥ አምልኮተ እግዚአ ብሔርን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ባደረጉት ትግል በሚታወቁት፣የእግዚአብሔርን ካህናትና ነቢያት በመብራት እያደኑ በጨረሱት በአክአብና በኤልዛቤል ዘመን፣ ታላቁ ነቢይ ኤልያስ እንኳ “ብቻዬን ቀርቻለሁ፣ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ውሰደኝ” እስከ ማለት ደርሷል። ሆኖም በዚያ እጅግ አስጨናቂ ዘመን በዚያው በአክአብና በኤልዛቤል ቤተ መንግሥት ውስጥ ብዙ ነቢያትን ከእነርሱሠይፍ የታደገ አብድዩ የተባለ አንድ ሰው ነበር። ይህንንም እንዲህ ሲል ይናገራል፡- “...እኔም ባሪያህ ከትንሽነቴ ጀምሬ እግዚአብሔርን እፈራ ነበር። ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ባስገደለች ጊዜ፥ መቶውን የእግዚአብሔር ነቢያት ወስጄ አምሳ አምሳውንም በዋሻ ውስጥ ሸሽጌ፡ እንጀራና ውኃ የመገብኃቸው ይህ ያደርግሁት ነገር በውኑ ለጌታዬ አልታወቀህምን? ”/፩ነገ ፲፰ ፥ ፫-፲፫/

የእግዚአብሔር ነቢያትና ካህናት እየታደኑ በተጨረሱበት በዚያን ዘመን ያንን ባደረጉት በነገሥታቱ ቤተ መንግሥት ውስጥ አንድ መቶ ነቢያትን እንጀራና ውኃ እየመገበ ያተረፈ ሰው ካለ መንፈሳዊ ላለመሆን ከስንፍናና ከቁርጠኝነት ማነስ በስተቀር ሌላ ምንም ዓይነት ነገርን ምክንያት ለማድረግ አይቻልም ማለት ነው። አብድዩ በንጉሡና የመጨረሻ አረመኔና ጨካኝ በሆነችው በኤልዛቤል ዘንድ የሠራው ሥራ “ወሬው እንኳ ቢሰማ በነቢያተ እግዚአብሔር ላይ እንደ ደረሰው ያለ ከባድ መከራና ሞት ይደርስብኛል፣ ያለሁበት ቦታና ጊዜ እንዲህ ለማድረግ አይፈቅድልኝም፣ እኔ በዚህ ሁኔታ እያለሁ ምን ማድረግ እችላለሁ? የምሠራበትና የምኖርበት ቦታና ሁኔታ አላደለኝም፣ . . ." የሚሉና የመሳሰሉ ሌሎችንም የስንፍና ምክንያቶችን አንዳቸውንም ሳይደረድር በቁርጠኝነት ነቢያተ እግዚአብሔርን የመታደግ ሥራ ሠራ። እግዚአብሔርም ከአክአብና ከኤልዛቤል ዓይን ሰወረው። በአክአብና በኤልዛቤል ቤት ውስጥ እና በእነርሱ ዘመን እንኳ እንደዚያ ዓይነት ሥራ መሥራት ከተቻለ ከመንፈሳዊነት የሚያግድ ከዚያ የበለጠ ምን ሁኔታ ይኖራል?

ጌታችንን ይከተሉትና ያገለግሉት ከነበሩት ከቅዱሳት አንስት መካከል አንዷ፤ የሄሮድስ የጦር ኃይል አዛዥ የነበረውና ኩዛ የተባለው ሰው ሚስት ነበረች። “የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐናም ሶስናም ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር።” /ሉቃ፰፥፫/ ይህቺው የኩዛ ሚስት ጌታችን ከሞት ሲነሣ ትንሣኤውን አስቀድመው ካዩትና ለሐዋርያት ከመሠከሩት ቅዱሳት ሴቶች አንዷ ነበረች። “ቃሎቹንም አሰቡ፥ ከመቃብሩም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለዐሥራ አንዱና ለሌሎች ሁሉ ነገሩአቸው:: ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና፣ የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ” እንደ ተባለ። /ሉቃ.፳፬፥፰-፲/

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ቅዱሳን ሁሉ፣ ይልቁንም ከቄሣር ቤት የሆኑቱ ሰላምታ ያቀርቡ ላችኋል" በማለት ክርስቲያኖችን እንደ ጎመን ሲቀረድዱ በነበሩት በሮማውያን ቄሣሮች ቤትም እንኳ ሳይቀር ቅዱሳን እንደ ነበሩ በመልእክቱ ተናግሮአል። /ፊል.፩፥፳፪/ እነዚያን በቄሣር ቤት የነበሩትን ቅዱሳን በሰላምታ ዓይነት ሁኔታ ያስታወሳቸው ያለ ምክንያት አልነበረም። ክርስቲያኖች በነጻነት እግዚአብሔርን ማምለክ አይችሉባቸው

በነበሩት ዘመናት በመሬት ውስጥ (በግበበ ምድር)፣ በዋሻዎችና በመሳሰሉት ሁሉ ሃይማኖታቸውን ይጠብቁና አምልኪቸውን ይፈጽሙ ነበር።

እንደዚያ አስቸጋሪ በነበሩ ሁኔታዎች በአክአብና በኤልዛቤል ቤተመንግሥት ውስጥ፣ በሄሮድስ ቤተ መንግሥት ውስጥ፣ በቄሣሮች ቤተመንግሥት ውስጥ መንፈሳዊነት የሚቻል ከነበረ በሌላ በምን ሁኔታ አይቻልም ሊባል ይችላል? ስለዚህ በሁኔታዎችና በዘመኑ እያሳበብን ስንፍናችንን ለመሸፈን ከምንሞክር ለቆረጠና ለወሰነ ሰው ከመንፈሳዊነት የሚያግድ ምንም ነገር እንደሌለ በመገንዘብ ራሳችንን ለመንፈሳዊነት ማዘጋጀትና እግዚአብሔር እንዲረዳንና ኃይሉንና ብርታቱን እንዲሰጠን መማጸን ይገባናል።

፭. መንፈሳዊነት የኑሮ ሁኔታ የማይወስነው ነው።

ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪ መንፈሳዊነትን ድህነት፣ ሀብታምነት፣ ተራ ሰውነት፣ ንጉሥነት፣ የሥራ ዓይነት (ግብርና፣ ንግድ፣ ውትድርና፣ሚኒስትርነት ወዘተ) የማያግደውና የማያስቀረው ነው። ጌታችን በልደቱ በረከት ያሳተፋቸው ሰብአስገልና እረኞቹ በዚህ ዓለም ማኅበራዊ ሕይወትሁለቱ ጠርዞች (ጫፎች) ናቸው። ሰብአ ሰገል ነገሥታት እንደ መሆናቸው በዚህ ዓለም መዓርግና ሥልጣን የመጨረሻውን ከፍተኛ ደረጃ ሲይዙ እረኞቹ ደግሞ የመጨረሻውን ዝቅተኛ ደረጃ የያዙ ናቸው። እነዚህ ከመጨረሻው ከፍተኛና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበሩት በበረከተ ልደቱ ከተሳተፉ፤በእነዚህ መካከል ያለ ሌላው ሁሉ ላለመሳተፍ ምክንያት የለውም ማለት ነው። በሠረገላው ላይ ተቀምጦ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዱ የሆነውን ትንቢተ ኢሳይያስን ሲያነብ የነበረውና በመንፈስ ቅዱስ ላኪነት በሐዋርያው በቅዱስ ፊልጶስ ሐዋርያነት ወንጌል ተሰብኮለት፣ በፈቃዱ አምኖ፣ተጠምቆ፣ ክርስትናን ተቀብሎ ደስ ብሎት ወደ ሀገሩ የመጣውና ለሀገሩ ሕዝብም ሐዋርያ መሆኑ የተመሰከረለት ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የንግሥት ህንደኬ የገንዘብ ሚኒስትር ነበር። /የሐዋ፰፥፳፯-፴፱/

በመቄዶንያ ሀገር በፊልጵስዮስ ከተማ ቅዱስ ጳውሎስ የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልቧን የከፈተላትና አምና ከነቤተሰቦቿ የተጠመቀችው ልድያ የሚሏት ሴት ሐር ሻጭ ነጋዴ ነበረች። /የሐዋ፲፮፥፲፬-፲፭/

በአንድ ወቅት ታላቁ ቅዱስ እንጦንዮስ “እንደ እኔ አድርጎ እግዚአብሔርን የሚወድደውና የሚያገለግለው ሌላ ሰው ይኖር ይሆን?” የሚል ክፉ ሐሳብ በውስጡ እየመጣ ባስቸገረው ጊዜ እግዚአብሔር በቤተመንግሥት ውስጥ ወደ ነበረ አስካፍ ወደ ተባለ ጄኔራል ላከው። ወደዚያም ሄዶ አስካፍ ስለሚባለው ሰው በጠየቀ ጊዜ ታሞ ተኝቶ አገኘው። ቅዱስ እንጦንዮስም “ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን አኗኗር ንገረኝ” ቢለው “እኔ በቤተ መንግሥት ውስጥ በታላቅ ሥልጣን የምኖር ሥጋዊ ሰው ነኝ፣ ለአንተ የሚነገር ምን ነገር አለኝ ብለኽ ነው?” አለው። በዚያን ጊዜም ቅዱስ እንጦንዮስ “እኔ የመጣሁት ከእግዚአብሔር ታዝዤ ነውና እባክህ ንገረኝ” አለው። አስካፍም ነገሩ ከእግዚአብሔር መሆኑን ሲረዳ “እኔ በቤተ መንግሥት የምኖር ሰው ነኝ፣ ግን በወገቤ ለሰውነት የሚሸክርና የሚያስጨንቅ ትልቅ ሠቅ ታጥቄ የጌታዬን ሕማምና መከራ ሳስብ እኖራለሁ። ግን አንድ ወቅት አጃቢዎቼ ወታደሮች ነክተውኝ ሠቁ ወደ ሰውነቴ ውስጥ ገብቶ አቁስሎኝ አሁን እንደምታየኝ ታምሜ ተኝቻለሁ” በማለት ሕይወቱን ነገረው። በዚያን ጊዜ ቅዱስ እንጦንዮስ “ይህ ሰው እንኳ በቤተ መንግሥት በታላቅ ሥልጣን እየኖረ እንዲህ ያለ ገድል ካደረገ እኔ በበረሓ እየኖርኩ ምን እግዚአብሔርን አገለገልኩ እላለሁ?” በማለት ትሕትናን ተምሮ ሄዷል።

ስለሆነም መንፈሳዊነት ሁኔታና ቦታ፣ የሥራ ዓይነትና ዘመን የማያግደው ወደ እግዚአብሔር የሚደረግ ጉዞና በቸርነቱ የሰጠንን የቅድስና ባሕሪያት ገንዘብ ለማድረግ የሚደረግ መሰላላዊ ዕድገት ስለሆነ በዚህ መንገድ ለመጓዝና ለማደግ እንድንችል እግዚአብሔርን እንማጸነው።የእመቤታችን አማላጅነት፣ መንፈሳውያን የሆኑ ቅዱሳን ሁሉ ጸሎትም ይርዳን፣ አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር